


# አስከፊውን ስርዓት ለማስወገድ
# ጠንካራ የጋራ ትግል ያስፈልጋል!

የኢትዮጵያ ህዝብ በሕ.ወ.ሓ.ት./ኢሕአዴግ ግፈኛ ስርዓት እየደረሰበት ያለዉ ግፍ እስራትና ግድያ እየተባባሰ መምጣቱ የሚያጠያይቅ ስላልሆነ የሙብት የነጻነትና የሀገራችን ሉዓላዊነት ትግል ከመቸዉም ጊዜ በበለጠ መጠናከር አለበት።

ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን በተደጋጋሚ አያሌ ጠላቶች አንበርክከዉ ያስረከቡንን ዉድ አገራችን ኢትዮጵያ በተባበረ ክንዳችን ፅናታችንና አንድነታችንን መጠበቅና መከላከል አለብን፡ ዜግነታዊ ግዴታችንም ነዉ።

ከዚህ ድንቅ ጀግና ህዝብ ተወልደን ህዝባችን ሲረገጥ ንብረቱ ሲዘረፍ የህግ የፍትህ ያለህ ሲል ከዛም አልፎ ዳር ድንበራችን ሲደፈር ባይተዋር ሆነን ዝም ብሎ መመልከት አግባብነት የሌለዉና አሳፋሪ ድርጊት ነዉ።

የኢትዮጵያ ጠላቶች በቋንቋ በጎሳና በሀይማኖት ከፋፍለዉ እርስ በራሳችን ለማጨፋጨፍና እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ኣይነቱ ኣካሔዳቸዉን እጅ ለእጅ ተያይዞ በህብረት ተፋልሞ ማክሰምና በምትኩ አንድነትንና መከባበርን ያካተተ ኢትዮጵያዊ ስሜትና ወኔ መስፈን አለበት። ስለዚህም አገር ኣድን አንቅስቃሴ መደረግ አንዳለበት በፅኑ አናምናለን።

የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችም የህዝቡን አጀንዳ በማስቀደም የእርስ በርስ ያለመግባባቱን ትተዉ ልዩነታቸዉን እያጠበቡ የመቀራረብና አብሮ የመስራትን እንቅስቃሴ አጠናክረዉ እንዲቀጥሉ እናሳስባለን።

እንዲሁም በመሳሳት በጥቅምና በጭፍን ዘረኝንት ከአረመኔዉ ሕ.ወ.ሓ.ት ጎራ ተሰልፋሁ አገርንና ህዝብን የሚጎዳ ህገ ወጥ ድርጊቶች በመፈጸም ያላችሁ ሁሉ፡ የጊዜ ጉዳይ እንጂ የወያኔ ስርዓት መገርሰሱ አይቀርምና ህዝባችን በማካሄድ ላይ ያለዉን የሙብትና የአገር ሉዓላዊነት የማስከበር ትግል ጎን ትሰለፉ ዘንድ አሁንም ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባልን።

ጋሻ ለኢትዮጵያዉያን ይህ የሕ.ወ.ሓ.ት./ኢሕአዴግ አስከፊ አገዛዝ ከስሩ ተነቅሎ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚበጅ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እስኪገነባና የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ፍጹም እስኪከበር ድረስ ለትግሉ የምናበረክተዉ አስተዋፅአኦ ይቀጥላል።

*ኢትዮጵያ በልጆችዋ የተባበረ ሀይል ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!*
*ጋሻ ለኢትዮጵያዉያን*

***November 3, 2014***